# ማሳሰቢያ ለኅብረተሰቡ

## ሁሉንም የርስዎን የፌዴራል መንግሥት የሕክምና ኢንሹራንስ ያገኛሉን?

# ከጃንዋሪ 1, 2007 እስከ ማርች 31, 2007

ይህ የመመዝገቢያ የጊዜ ገደብ **ለፌዴራል መንግሥት የሕክምና ርዳታ 'ሀ' ና 'ለ' (Medicare part A and part B)** የተሰጠ ነው።

(የመንግሥታዊ የሕክምና ርዳታ ወይም የሜዲኬር ካርድ ቀይ -ነጭ - ሰማያዊ ምልክት ያለበት የፌዴራል የጤና ኢንሹራንስ ነው።)

**** የዕድሜዎ 65 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የፌዴራል የጤና ኢንሹራንስ ሊያገኙ ይችላሉ፣ በተጨማሪም፡-**

* የአሜሪካ ዜጋ ከሆኑ ወይም በሕጋዊነት አሜሪካ የገቡና ሕጋዊ የጊዜ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፈቃድ ያለዎትና በአሜሪካ ያለማቋረጥ በተከታታይ ላለፉት አምስት ዓመታት ከኖሩ ይህን የፌዴራል የጤና ኢንሹራንስ ሊያገኙ ይችላሉ።

ሁሉንም የርስዎን የፌዴራል መንግሥት የሕክምና ኢንሹራንስ (እርዳታ) ያገኛሉን? የQMB ፕሮግራም (መመዘኛውን ላሟሉ የሚገባ የተጠቃሚዎች የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ ፕሮግራም) የርስዎን ወርሃዊ ክፍያ ሊከፍል ይችላል።

---

## ዕድሜዎ 65 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነና የፌዴራል መንግሥት የሕክምና ኢንሹራንስ ከሌለዎት፡-

ዕድሜዎ 65 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነና የአሜሪካ ዜጋ ከሆኑ ወይም በሕጋዊነት አሜሪካ የገቡና ሕጋዊ የጊዜ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፈቃድ ያለዎትና በአሜሪካ የገቡና ሕጋዊ የጊዜ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፈቃድ ያለዎትና በአሜሪካ ያለማቋረጥ በተካታታይ ላለፉት አምስት ዓመታት ከኖሩ ምናልበትም ለፌዴራል መንግሥት ለሁለቱም የሕክምና ኢንሹራንስ 'ሀ' ና 'ለ' (Medicare Part A and Part B ) ቀይ ነጭና ሰማያዊ ካርድ ሊያገኙ ወይም ሊገባዎት ይችል ይሆናል፡፡

ሥራ ያልሠሩ በርካታ ሕዝቦች እንዳዚሁም በዚህ የተነሳ ከደመወዛቸው ለሕይወት ዋስትና (Social Security ) የሚቆረጥ ቀረጥ ስላልከፈሉ የፌዴራል የጤና ኢንሹራንስ 65 ዓመት ሲሆናቸው ሊያገኙ ወይም ላያገኙ እንደሚችሉ ላያውቁ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴም የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ ለማግኘት በየወሩ ከፍተኛ ክፍያ ርዳታ ፈላጊዎች እንደሚከፍሉ ይነገራቸዋል፡፡ የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ ለማግናት ከፍተኛ የወር ክፍያ መክፋሉ በዚህ ሁኔታ እውነት ቢሆንም በርካታ ተጠቃሚዎች ለክፍለሃገሩ የሕክምና ርዳት (State Medicaid Program) ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ መመዘኛውን ካሟሉ የQMB ፕሮግራም ወርሃዊ ክፍያዎን እንዲከፍሉ በማድረግና ሌላ ወጭን በመክፈል የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ "ሀ" ና "ለ" ን (Medicare Part A and part B ) ሌላ ወጭ ሳይኖሮት ይህን የተጠቀሰውን ኢንሹራንስ እንዲያገኙ ይረዳዎታል፡፡

ዕድሜዎ 65 ወይም በላይ ከሆነና ሁለቱም የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ " ሀ" ና "ለ" (Medicare part A and part B) ወይም (የሆስፒታል የሕክምና ኢንሹራንስ) ከሌለዎት ለእርዳታ ማመልከቻ የሚከተሉትን የደረጃ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርቦታል፡-

## 1ኛ እርምጃ፡- ለፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ (Medicare) በሕይወት (ኀብረት) ዋስትና አስተዳደር

**(Social Security Administration) ማመልከቻ ያቅርቡ።**

ያሳታውስ የሕይወት (ኀብረት) ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) አስተርጓሚ ከስፈለግዎት የመስጠት ወይም የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። አስተርጓሚ ለማግኘት ችግር ካለብዎት (ማለትም በአስተዳደሩ ጽሕፈት ቤት ሲቀርቡ ወይም በስልክ ሲነጋገሩ) የሕይወት (ኀብረት) ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) የሥራ መመሪያቸውን (Policy) ትርጉምን በተመለከተ ይጠይቁ ይህም የትርጉም የሥራ መመሪያ (Policy) ማስተርጎምን በተመለከተ በGN00203011 በልዩ የአጠያየቅ ሁኔታ የተወሰነ (ዝቅተኛ) የቋንቋ ችሎታን ለተጠቃሚዎች በሚያመለክት አንቀጽና በቃንቃ ችሎታን ለተጠቃሚዎች በሚያመለክት አንቀጽና በቋንቋ ትርጉም ርዳታ ክፍል አስተዳደሩ እንዲመለከት በጥያቄዎ ያክሉበት።

በዚህ የምዝገባ ወቅት የጊዜ ገደብ ወደ የሕይወት (ኀብረት) ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) ጽሕፈት ቤት ይሒዱ። የጊዜ የምዝገባ ገደብ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

* የርስዎ "የመጀመሪያ የመመዝገብያ የጊዜ ገደብ" የመመዝገቢያ የመጀመሪያ ጊዜዎ በተለምዶ የሚጀምረው ዕድሜዎ 65 ዓመት ሊሆነው ሲል ከሦስት ወራት በፊትና ከ65 ዓመት ሦስት ወር በኃላ ነው ይህም ማለት 3 ወር ከልደት ቀንዎ 3ወር በፊትና በሓላ ማለት ነው ። (ለአንዳንድ የሕዝብ አካላት ከ65 ዓመት በላይ 7 ዓመትን የመመዝገቢያ ገደቡ ሊያጠቃልል ይችላል ይህንንም አጠቃሎ አመልካቹ ግለሰብ የአሜሪካ ዜጋ ወይም በሕጋዊነት አሜሪካ የገባና ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፈቃድ ያለው በአሜሪካ ያለማቋረጥ በተከታታይ ላለፍት አምስት ዓመታት ከኖረ ይሆናል።

* ሁሉም (ማንኛውም) "አጠቃላይ የመመዝገቢያ ገደብ፡- ለፌዲራል የሕክምና ኢንሹራንስ "ሀ" ና "ለ" (Medicare part A and Part B) የመመዝገቢያ ጊዜ በያመቱ ከጃንዋሪ 1 እስከ ማርች 31 ይሆናል።

በሥራዎ የዓመታት ታሪክ ባለቤትዎ የፌድራል የሕክምና ኢንሹራንስ ለማግኘት በቂና ተገቢውን ጊዜ ከልሠሩ ወይም ይህ የፌዲራል ኢንሹራንስ የማይገባዎት ከሆነ የሕይወት ዋስትና አስተዳደር ተጠሪ (Social Security Administration Representative ) ለወርሃዊ የሆስፒታል ኢንሹራንስ ክፍያ ክፍል "ሀ" እና ለሕክምና ኢንሹራንስ ክፍል "ለ" (Premium Hospital Insurance" Part A and Medical Insurance Part B) ማመልከቻዎን መቀበል ይኖርበታል፡፡ ለክፍል "ሀ" ቅድመሁኔታ ላለው ጊዜያዊ ምዝገባ ለሆስፒታል ኢንሹራንስ (Conditional Enrollment " In Part A Hospital Insurance )ለመመዝገብ መጠየቅ ይኖርብዎታል፡፡

ለክፍል "ሀ" ( Part A) ቅድመ ሁኔታ ያለው ጊዜያዊ ምዝገባ ሲያደርጉ የሆስፒታል ኢንሹራንስ እንዲፈቀድልዎት የሚሆነው የክፍለሃገሩን (State) የወርሓዊ የክፍያ መመዘኛ ከላይ እንደተጠቀሰው የQMBን ፕሮግራም ሲያሟሉ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እርሶዎና ቤተሰብዎ ወርሕዊ የሜዲኬር ወይም የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ (Medicare) መክፈል ከቻሉ ለክፍል "ሀ" ና "ለ" በክፍያው መሠረት ለመመዝገብ ይፈልጉ ይሆናል፡፡

የሚገናኙት የሕይወት (ሕብረት) ዋስትና አስተዳደር ተጠሪ (Social Security Representative) ከማመልከቻው ጋር የተያያዙትን ግንዛቤዎችና አሠራሮች እንግዳ ከሆነበት ወይም ካልተረዳ የሚከተለውን የሕይወት (ሕብረት) ዋስትና ፖሊሲዎች እንዲመለከት ይጠይቁ፡፡ ፖሊሲውም በHI 00801.126; HI00801.131; HI00801.137; እና HI00801.140 አንቀጾች ላይ ተብራርቷል፡፡ የሕይወት (ሕብረት) ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) የርሶዎን የሜዲኬር ማመልከቻ ሳይቀበል ሊያስናብትዎት አይችልም፡፡

የሕይወት (ሕብረት)ዋስትና አስተዳደርን (Social Security Administration) ጽሕፈት ቤት ሲለቁ (ሲሰናበቱ) ለሜዲኬር የ "ሆስፒታል ኢንሹራንስ "ክፍለ ሀ (Part A) እና ለሜዲኬር የ"ሕክምና ኢንሹራንስ" ክፍል "ለ" እንዳመለከቱ ማረጋገጫ ወይም ደረሰኝ መቀበል ይኖርቦታል፡፡

**2ኛ እርምጃ፦ ለQMB ፕሮግራም (መመዘኛውን ላሟሉ የሚገባ የፌዴራል ኢንሹራንስ ፕሮግራም)**
**ለቤተሰብ ድጋፍ ግብረሠናይ ጽሕፈት ቤት (The Family Support Division) ማመልከቻዎን ያቅርቡ፡፡**

ለሜዲኬር ማመልከቻ ካቀረቡ በሐላ በ60 ቀናት ውስጥ ለሜዲኬር ሆስፒታል ኢንሹራንስና ለሕክምና ኢንሹራንስ የይገባኛል ማመልከቻ መልስ (ደብዳቤ) ያገኛሉ። ይህም ደብዳቤ ለሜዲኬር ጥቅም ወይም ብቃት ከየትኛው ወር እንደሚጀምሩ ይነግርዎታል። (ለምሳሌ ደብዳቤው እንመሚከተለው ሊመልስልዎት ይችላል፦ ከJuly, 2007 ጀምሮ የሜዲኬር ሆስፒታል ኢንሹራንስና የሕኪምና ኢንሹራንስ ይገባዎታል ወይም ያገኛሉ)።

ምንም እንኳ ደብዳቤው ሜዲኬር እንዲያገኙ ቢያሳይዎትም የሚኖሩበት ክፍለ ሃገር (State) በQMB ፕሮግራም ሥር የርሶዎን የሜዲኬር ወርሓዊ ክፍያ ካልከፈለ ሜዲኬር ላያገኙ ይችላሉ።

ክፍለሃገሩ (State) ወርሓዊ የሜዲኬር ክፍያ እንዲከፍልልዎት የተሰጠዎትን (የተላከለዎትን) የሜዲኬር ደብዳቤ ወደ አቅራቢያዎ በሚገኘው የክፍለሃገሩ የሕክምና ርዳታ ጽሕፈት ቤት ወይም የቤተሰብ ገብረሠናይ ጽ/ቤት (Family Support Division) በመውሰድ ለQMB (መመዘኛውን ለሟሉ የሚገባ የፌዴራል ኢንሹራንስ ፕሮግራን) ጠቀሜታ ለማመልከቻ ያቅርቡ። ከዚህ በፊት በክፍለ ሃገሩ ፕሮግራም የሚሰጥ የሕክምና ርዳታ ወይም ኢንሹራንስ (Medicaid) ካለዎት (ቀይ ካርድ) በሜዲኬድ መሠረት የQMB የሕክምና ጠቀሜታ ለማግኘት ሊጠይቁ ይችላሉ።

ሆኖም የክፍለሃገሩ (State) ተጠሪ የQMB የማመልከቻ ፖሊስና አሠራር እንግዳ ከሆነበት (ከሆነባት) ተጠሪውን ወይም የተጠሪውን አለቃ ስለቤተሰብ ድጋፍ ግብረሠናይ ጽሕፈት ቤት በገቢ ይዞት ፖሊሲ (Family Support Division Income Maintenance Policy) መዝገብ አንቀጽ፦ 0865.020.00 እስከ 0865.020.15 የተደነገገውን እንዲመለከቱ ይጠይቁ። ተጠሪው (ተጠሪዋ) የእርሶዎን QMB ማመልከቻ ሳይቀበሉ ሊያሰናብትዎት አይችሉም።

በክፍለሃገሩ (State) የሚሰጥዎት የሕክምና ኢንሹራንስ (Medicaid) ካለዎትና ያለዎት ከሆነ ሁሉም የራስዎ መለያ (ስም አድራሻ እድሜ ሶሻያል ሲኩሪቲ ወዘተ) በወቅቱ ተመዝግቦ ያለው አሁንም ያልተለወጠ ከሆነ የመንግሥት ተጠሪ ወይም የርሶዎን ጉዳይ የያዙት ሠራተኛ የQMB ማመልከቻውን ካለምንም ማዘግየት በቀጥታ ለጠቀሜታዎ ሊያፀድቁ ይችላሉ። ሜዲኬድ ከሌለዎት ወይም በሜዲኬድ ካልተመዘገቡ ሠራተኛው ማመልከቻዎን በመቀበል ለየትኛው የክፍለሃገሩ (State) የሕክምና ጠቀሜታ ወይም ኢንሹራንስ ተገቢውን መመዘኛ አሟልተው እንደሚያገኙ መግለፅ ይኖርባቸዋል። ሠራተኛው ከርሶዎ የመለያ መረጃ ሊጠይቁ

ይችላሉ፣ ይህም የባንክ ሒሳብ የሕይወት ወይም የቀብር ኢንሹራንስና የመሳሰሉትን ሊያጠቃልል ይችላል። የተጠየቁትን ሁሉ ሟሟላት እንደለብዎት ይገንዘብ። ነገር ግን የመንግሥቱ ተጠሪ ያሌለዎትን መረጃ ከጠየቁ ተጠሪውን (ተጠሪዋን) በመጥራት ወይም በደብዳቤ ወይም ቀጠሮ በመውሰድ በአካል በመገናኘት መርጃው እንደሌለዎትና መረጃውን ለማግኘት እርዳታ ይጠይቁ። የክፍለሃገሩ (State) ጽሕፈት ቤት የርሶዎን የQMB ሜዲኬድ ማመልከቻ በ45 ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ ይኖርቦታል።

**<u>3ኛ እርምጃ ስለማመልከቻዎ የክፍለሃገሩን መሥሪያ ቤት (State Agency) "ሀ" ና "ለ" ን የያዘ የሜዲኬር ካርድ (Medicare Card with both Part A and Part B ) እስከሚያገኙ ድረስ ጉዳይዎን ይከታተሉ።</u>**

ለQMB ጠቀሜታ ከማመልከቻዎ 50 ቀን ጀምሮ አወንታዊ መልስ ማግኘትዎን ያረጋግጡ። ከዚያም በሕላ የQMB አወንታዊ መልስ ከገኙ ከ90 ቀን በኃላ ከሕይወት (ሕብረት) ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) ለሜዲከር ርዳታ ጠቀሜታ እንደሚያገኙ የሚዙሪ ስቴትም ወርሃዊ ክፍያዎን እንደሚከፍልልዎት የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል። ሜዲኬር "ሀ" ና "ለ" (Medicare part A and Part B ) እንደተቀበሉ ያረጋግጡ። አዲስ የሜዲከር ካርድ ቀይ ነጭና ሰማያዊ ያለበት ካርድ ማለትም ሁለቱንም ሜዲኬር "ሀ" ና "ለ" ን የያዘና ጠቀሜታውን የሚዘረዝር ካርድ ይቀበላሉ።

አዲስ የሜዲኬር ካርድ ና ከሶሻያል ሲኩሪቲ አስተዳደር ክፍለሃገሩ (ስቴት) የሁለቱንም የሜዲኬር የወር ክፍያዎች እንደሚከፍል የሚያስረዳ ደብዳቤ ካልተቀበሉ የሜዲኬድን የመንግሥት ተጠሪ (የርሶዎን ሠራተኛ) ጃፈርሰን ሲቲ ያለውን የፕሮግራምና የፖሊሲ ጽ/ቤት ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ እንዲያነጋግሩ ይጠይቁ። የፕሮግራም ፖሊስ ጽ/ቤት ችግሩ መፍትሔ ካገኘ በሓላ ደብዳቤ እንዲጽፍልዎት ይጠይቁ።

በማንኛውም ጊዜ የስቴቱ የቤተሰብ ድጋፍ ግብረሠናይ ጽሕፈት ቤት (Family Support Division) በሚወስነው ውሳኔ ወይም በሚወስደው እርምጃ ካልተስማሙ ለሚዛናዊ የችሎት ስሞታ (Fair Hearing) ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ የመጠየቅ መብት አለዎት ። ከመንግሥቱ ተወካይ አለቃ ጋር ለመገናኘት ወይም ለመነጋገር መብት አለዎት።

**<u>ስለQMB (መመዘኛውን ላሟሉ የሚገባ የተጠቃሚዎች የፌዴራል የሕክምና ኢንሹራንስ ፕሮግራም)</u>**

QMB ልዩ የሆነ የርስዎን ወርሓዊ የሕክምና (የMedicare) ክፍያ የሚከፍል ፕሮግራም ነው፣ ይህም ለሜዲኬር የሚገባውን የርሶዎን የሓላፊነት የክፍያ ድርሻ (deductibles) ና ከኪስዎ ለሕክምና የሚከፍሉትን ለሜዲኬር ግልጋሎት ተገቢውንና ሕጋዊውን ትመና የሚያጠቃልል ፕሮግራም ነው። በሚዙሪ የQMB የኢንሹራንስ ሽፋኔ ለበርካታ የሕክምና ሁኔታዎች የሚከፍልና የስቴቱ ሜዲኬድ የማያጠቃልለውን የሚሸፍንና እንደዚሁም ሜዲኬይድ በሕጉ መሠረት የሚተካ ፕሮግራምም ነው። ዶክተሩ ክሊኒኩ ወይም ሆስፒታሉ (ግልጋሎት ሰጪው አካል) ሁለቱንም ሜዲኬርና ሜዲኬይድ ወይም ሜዲኬር እና QMB እስከተቀበሉ ድረስ በአብዛኛው መልኩ በመንግሥታዊ ኢንሹራንሱ የተሸፈኑ ነዎት።

## <u>QMB ለማግኘት መመዘኛዎች፡-</u>

* የአሜሪካ ዜጋ የሆኑ ወይም መመዘኛውን ያሟሉ የአሜሪካ ዜጋ ያልሆኑ
* በሚዙሪ ነዋሪ የሆኑ
* ሶሻያል ሴኩሪቲ ያላቸው
* በክፍል "ሀ" ሜዲክር (Medicare Part A) የተመዘገቡና ርዳታ የሚያገኙ ወይም በገድብ በጊዜያዊነትና በሁኔታቸው የተመዘገቡ።
* አጠቃላይ ንብረታቸው $4,000 (ለነጠላ) $6,000 (ላገቡ) የሆነ(አንዳንድ ንብረቶች ላይቆጠሩ ይችላሉ፣ ይህም ወደ ዶክተር ዘንድ ለመሄድ የሚያስፈልግ መኪና ወይም መኖሪያ ቤት) ያጠቃልላል።
* የወር ገቢ $817 (ለነጠላ ) ወይም $1,000 (ላገቡ) (ለ2006 የወር ገቢ ጣሪያ አለ እነዚህ የገቢጣሪያዎች በየዓመቱ በአፕሪል (April) ወር ይጨምራሉ)።

## <u>አብዛኛውን ጊዜ ሜዲኬር ለማግኘት የሚከሠቱ ችግሮችና አንዳንድ የመፍትሔ ጥቆማዎች።</u>

## <u>ሚዲኬር ክፍል "ሀ"ን (Medicare Part A) ወርሓዊ ክፍያን በየወሩ የዕዳ ደብዳቤ ከተላከሌዎትና መቀበል ከጀመሩ፡-</u>

ሜዲኬር ክፍል "ሀ" ን ወርሓዊ ክፍያን በተመለከተ በየወሩ የዕዳ ደብዳቤ ከተላከልዎትና መቀበል ከጀመሩ የሕይወት (ሕብረት) ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) የርሶዎን ክፍል "ሀ" (Part A) መቀሜታ ከክፍለሃገሩ (State) አሠራር ጋር በማያያዝ ከስቴቱ ክፍያ ጋር ቅደመ ሁኔታውን አላዘጋጀም ቀይም አላበጃጀም ማለት ነው፡፡ ይህን ችግር ለማሰወገድ ወደ ሶሺያል ሴኩሪቲ አስተዳደር ጽ/ቤት ይሒዱ፡ ሲሄድም የዕዳውን ወርሓዊ ደብዳቤ በእማኝነት ያቅርቡ፡፡ ይዘው ይሒድ፡ ሲያስረዱም ስህተት እንደተሠራና ሲመዘገቡም ለክፍል "ሀ" (Part A) በቅድመ ሁኔታው መሠረት ጠይቀው እንደሆነ ያስረዱ፡፡ ለሶሻያል ሴኩሪቲ አስተዳደር ተጠሪውም የቅድመ ሁኔታ ምዝገባን በተመለከተ የሚከተሉትን የፖሊሲ አንቀጽ የሚያጠቃልሉትን ያስታውሷቸው HI00801.126, HI00801.137, and HI 00801.140::

በትክክልና ቅደመሁኔታውን በሟሟላት በክፍል "ሀ" ሜዲኬር (Medicare Part A) ከተመዘገቡ የሕክምናዎ ርዳታ ቁጥር ከZ99 ኮድ (ወይም መለያ ቁጥር) ጋር በሶሺያል ሴኩሪቲ ኮምፒወተር የአሓዝ አሰያየምና አሠራር ጋር ይታያል፡፡ ስቴቱ ይህን የሶሺያል ሴኩሪቲ ኮድና የቅድመ ሁኔታ አመዘጋገብ ሁኔታ በትክክል ካላየ ወርሓዊ ክፍያዎን አይከፍልም፡፡ የሚዙሪ ስቴት የርሰዎን ወርሃዊ ክፍያ መክፈል ሲጀምር ኮዱ ወይም መለያ ቁጥሩ ወደ526 ይቀየራል፡፡ ካስፈለገም ለተጠሪው አለቃ ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ ለማነጋገር ይጠይቁ፡፡

**<u>ስቴቱ የርስዎን QMB ካፀደቀ በኃላ ነገር ግን ከሶሺያል ሴኩሪቲ አስተዳደር ክፍል "ሀ" ን (Part A) የሚሸፍን የማረጋገጫ ደብዳቤ ካላገኙ፡-</u>**

ስቴቱ የርሶዎን QMB ካፀደቀ በሓላ ነገር ግን ካሶሺያል ሴኩሪቲ አስተዳደር ጽ/ቤት ስቴቱ የርሶዎን ወርሃዊ ክፍያ እንደሚከፍል (ማለትም ለክፍል "ሀ" (Part A) የማረጋገጫ ደብዳቤ ካለከልዎት ምናልባትም ስህተቱ ኮምፒወተር አሠራር ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህን ችግር ለማስወገድ የቤተሰብ ድጋፍ ግብረሠናይ ጽ/ቤት (Family Support Division) የተጠሪውን አለቃ ይገናኙ፡፡ QMB ቢኖሮትም ስቴቱ ለክፍል "ሀ" (Part A) ወርኃዊ ክፍያ እንዳልከፈለልዎት ያስረዱ፡፡

በጄፈርስን ሲቲ የሚገኘውን የግዢ ንዑስ ክፍል (buy in unit) እንዲያነጋግሩና ከዚያም በኃላ ስለችግሩ

መፍትሔና ችግሩ ከተፈታ በኃላ የጽሑፍ ማረጋገጫ እንዲላክልዎት ይጠይቁ፡፡ የአስተዳደሩ ተጠሪ አለቃም እርሶዎን በዚህ መንፈድ ለመርዳት ፈቃደኛ ካልሆኑ የእርሳቸውን አለቃ ላማነጋገር ይጠይቁ መልሳው ለርሳቸውም የመጀመሪያውን አንድ ዓይነት ጥያቄ ይጠይቁ ፡፡ በተጨማሪም ሠራተኞቹ ለችግሩ መፍትሔ ካላገኙ ነገሩ በችሎት እንዲታይልዎት የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡ በማንኛውም ጊዜ ማንማንን እንዳነጋገሩ በመዝገብዎ(በማኃደርዎ) ፅፈው በሪኮርድ ይያዙ፡፡

**<u>ስቴቱ የርሶዎን የQMB ጥያቄ ካላፀደቀ ወይም ለውሳኔ መዝገብዎን ካላካተተ፡-</u>**

የመንግሥቱ ተጠሪ የQMB ጥያቄዎን ለመመለስ ወይም ለሚያገኙት ጠቀሜታያገቡትን ማመልከቻ ለመጨረስ የQMB ን ፕሮግራም ምናልባት ያልተረዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ችግሩን ለመፍታት ጉዳዩ በችሎት እንዲታይና በአለቃው እንዲመረመር መጠየቅ ይችላሉ፡፡ በርካታ የመንግሥት ተጠሪ ሠራተኞች የQMB ፕሮግራም እንዴት እንደሚሠራ አያውቁም፡ ስለሆነም ጉዳዮ አድሎዎ በሌለበት ችሎት እንዲታይሎትና የኬዝወርከርዎ አለቃ ጉዳዮን እንዲመርምሩና ለርሶዎም የተመደቡት ሠራተኞች የQMB ጉዳዮችን በተገቢው መንገዱ እንዲያስተናግዱ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ይጠይቁ፡፡

ለሜዲኬር ና ለስቴቱ ወርሓዊ ክፍያ የሚገባውን ኋሚሉና ጠቀሜታው የሚገባዎት ከሆነ የሆስፒታል ሜዲኬር ኢንሹራንስ እንደሚገባዎትና ጠቀሜታው እንዳለዎትና የሚዙሪ ስቴትም ወርሓዊ የሜዲኬር ክፍያ እንደሚከፍል የሚገልፅ ደብዳቤ ይቀበላሉ፡፡ በተጨማሪም አዲስ ቀይ ነጭና ሰማያዊ የሚዲኬር ካርድ ማለትም ሁለቱም የሆስፒታል ኢንሹራንስ (Part A) ና የሕክምና ኢንሹራንስ (Part B) እንዳለዎት የሚያረጋግጥ ይላክልዎታል፡፡

በነዚህ እርምጃዎች ሜዲኬርና QMB ለማግኘት ካልቻሉ ሕጋዊ እርዳታ ምሥራቅ ሚዙሪ የሕግ አገልግሎት የሕዝብ ጠቀሜታ እርዳታ ክፍል (Legal Services of Eastern Missouris Public Benefit Project) መፍትሔ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ሥልክ ቁጥሩም (314)256-8713 ነው፡፡